ኪታ ብሬመን
መንግስታዊ የብሬመን
ህጻናት እና ቤተሰብ መዓከል

ኪታ ህጻናት ክትትል
ኪታ መውዓለ - ህጻናት
ኪታ መዋያ
ኪታ መሰባሰቢያ
ኪታ ቤተሰብ

[Übersetzt in die Sprache Amharisch]

# የአጠቃቀም መመሪያ:

**በልጆች እና በቤተሰብ ማእከሎች ውስጥ የሕፃን እንክብካቤ ደንቦች**
**ከኪታ ብሬመን**
ከጥር 2023 ዓ.ም

## ለመጀመሪያ አስፈላጊ መረጃዎች

**ኩ.ኤፍ.ዜት ምንድን ናቸው?**

የብሬመን ክልል መውዓለ-ህጻናት አስተዳደር ለህጻናት እና ቤተሰብ መዓከል በአጭሩ ኩ.ኤፍ.ዜት (KuFZ) ተብሎ ይጠራል። ኩ.ኤፍ.ዜት ለህፃናት እና ለቤተሰቦች የተዘጋጁ ቦታዎች ናቸው። ኩ.ኤፍ.ዜቶች ህፃናትን ያስተምራሉ፣ ያሳድጋሉ እንዲሁም ይከታተላሉ።

**ለኩ.ኤፍ.ዜት ስራ አስፈላጊው ምንድን ነው?**

- ኩ.ኤፍ.ዜት ሁሉንም ሕፃናት እድገት፣ ለሕፃኑ ምቹ በሆነ መልኩ ያመቻቻል
- ኩ.ኤፍ.ዜት ከወላጆች ጋራ በህብረት ይሰራል። ውላጅ የሚለው ቃል፣ ሁሉንም ህጋዊ አሳዳጊዎች የሚወክል ነው። በዚህ ስር ለሳሌ ብቻቸውን የሚያሳድጉ እናቶች፣ አባቶች እንዲሁም ሃላፊነቱን ወስደው ህፃናቱን ቤታቸው ውስጥ የሚያኖሩ ማደጎ አሳዳጊዎች ወይም ቤተዘመዶችን ያጠቃልላል።
- ኩ.ኤፍ.ዜት በየክፍለ-ከተማዎቹ ውስጥ ከነዋሪዎቹ ጋር በህብረት ይሰራል።

ኩ.ኤፍ.ዜቶች ለቤተሰቦች አስፈላጊ ተጠሪዎች ናቸው። ለበለጠ መረጃ በ ቤተስብ መዓከሎ የሚገኘወን *ለህጻናት እና ለቤተሰብ መዓከል እድገት እስፈላጊዎቹ ነጥቦች („Rahmenkonzeption für die Entwicklung von Kinder- und Familienzentren“).* የሚለውን መጽሄት መመልከት ይችላሉ።

**የአጠቃቀም መርሃግብሩ ማንን ይመለከታል?**

የአጠቃቀም መርሃግብሩ የወላጆችን፣ የህጻናትን እንዲሁም የጎብኚዎችን መብት እና ግዴታ በዝርዝር ያጠቃለለ ነው።

## የህጻናት ጥበቃ እና ክትትል

**ለልጆ እንዴት አድርገው የጥበቃ እና ክትትል ቦታ ማዘጋጀት ይችላሉ?**

ለልጆ የጥበቃ እና ክትትል ቦታ ለማግኘት፣ ለዚህ የተዘጋጀውን ፎርም መሙላት እና ማስረከብ ይኖርቦታል።

ኩ.ኤፍ.ዜት መመሪያ የብሬመን ክልልን የምዝገባ ህግን ተሞርኩዞ የተዘጋጀ ነው።

ኩ.ኤፍ.ዜት ልጆን የመከታትያ ቦታ ካለው ያሳውቆታል።

**ቦታ እንዳለ የሚያረጋግጥ ፅሁፍ ሲደርሶት በሚቀጥሉት 14 ቀናቶች ውስጥ ቦታውን ለልጆ እንደሚቀበሉ በፊርማ ማረጋጥ ይኖርቦታል።**

ይህ ካልሆነ፣ ቦታው ለሌላ ሰው/ልጅ ተላልፎ ይሰጣል።

የፖስታ አድራሻ
KiTa Bremen
Auf der Muggenburg 5
28217 Bremen
ስልክ ቁጥር
0421-361 5700
ፋክስ
0421-361 59771
ኢ - ሜል
office@kita.bremen.de
ድህረ - ገጽ
www.kita.bremen.de
የከተማ ውስጥ ባቡር
ቁጥር 3 እና 5
ትራንስፖርት የሚቆምበት ቦታ
Eduard-Schopf-Allee
ኪታ ብሬመን
የክፍለከተማ
ህዝባዊ አገልግሎት ቢሮ
ብሬመን
ዋና ስራ አስኻሂያጅ
ቮልፍጋንግ ባልማን
ምክትል ስራ አስኻሂያጅ
ፔትራ ሱንሴሽ
Deutsche Bundesbank
Filiale Hannover
ኢባን ቁጥር
DE27 2905 0000
1070 6000 00
ቢክ ቁጥር
BRLADE22XXX
የቀረጥ ቁጥር
60/146/12457

**ለልጆ የሚሰጠው ክትትል በየትኛው ሰዓት እና ግዜ ነው የሚሆነው?**

ሕጻናት መውዓል-ህጻናት ወስጥ ሲመዘገቡ፣ ምዝገባው ሁልግዜ ለአንድ አመት የሚያገለገል ይሆናል። ይህ ማለትም ከ01.08 ጀምሮ እስከ 31.07 ድረስ ያለው ግዜ እንደ አንድ የመውዕለ-ህጻናት አመት ይቆጠራል ማለት ነው። ልጆ ቆይቶ ቤመዘገብ እንኳን፣ የመውዓለ-ህጻናት ቆይታው በ01.08 የሚጠናቀቅ ይሆናል።

የክትትሉ ቦታ ለአንድ አገልግሎት ብቻ የታሰበ ሲሆን፣ ይህ ማለትም ከተዘጋጁት ክትትልሎች ወስጥ ዓፅደ-ህጻናት (Krippe)፣ ለመውዓለ-ህጻናት (Kindergarten) ወይም የህጻናት ማዋያ (Hort) ውስጥ ለአንዱ ብቻ የተዘጋጀ ነው ማለት ነው። ልጆ የሚያገኘውም ቦታ ከተጠቀውሱት ቦታዎች ውስጥ ለአንዱ ብቻ እንዲሁም ለተወሰነ የግዜ መደብ ብቻ ይሆናል ማለት ነው።

**ቀጥሎ ለሚመጣው የመውዓለ-ህጻናት አመት ክትትሉን እንዴት ማራዘም ይችላሉ?**

ልልጆ ቦታውን ማራዘም የሚፈልጉ ከሆነ፣ **በየአመቱ እንደአዲስ** የምዝገባውን ፎርም መሙላት እና ማስረከብ ይኖርቦታል። ወረቀቱን ከተቀበሉ በውሃላ በ14 ቀናት ውስጥ ፎርሙን ሞይልተው፣ ቦታውን ለልጆ እንደሚፈልጉ በፊርማዎት ማረጋገጥ አለቦት።

ለልጆ ክትትል የምግኘት መብት ካሎት፣ ልጆ ከነበረበት ኩ.ኤፍ.ዜት ክትትል ቦታ ይሰጠዋል። ይህ በመውዓለ-ህጻናቱ እና አጸደ-ህጻናት ስር ላሉ ልጆች የሚያገለግል ነው።

**በክትትሉ ገዜ የልጆን ሃላፊነት የሚሸከመው ማን ነው?**

ውላጆች ልጆቻቸውን ብክትትል ስር ሲሆኑ እንዲሁም በግሩፕ ወደ ሽርሽር ሲሄዱ፣ ሃላፊነቱ በኩ.ኤፍ.ዜት ስር ይሆናል። ይህ ሃላፊነት በህዝብ መብት እና ህግ መጸሃፍ ወስጥ *አንቀጽ § 1631 ይዝባር 1* ስር በዝርዝር ተጽፉዋል።

## የስራ ሰዓታት፣ ብዓላት እና ድንገተኛ አገልግሎት

**ልጆ በማንኛውም ሰዓት ወደ ኩ.ኤፍ.ዜት መውዓለ-ህጻናት መሄድ ይችላል?**

ኩ.ኤፍ.ዜት. ከሰኞ እስከ አርብከ8:00 እስከ 16:00 ሰዓት ክፍት ነው። ግዚያዊ ይህጻናት ማቆያ ከሰኞ እስከ አርብ ከ13:00 – 16:00 ክፍት ነው። የስራ ሰዓቶችን በተመለከተ ኩ.ኤፍ.ዜት ከወላጆች ኮሚቴ ጋራ በተከታታይ ይነጋገራል።

እያንዳንዱ የኩ.ኤፍ.ዜት ተቋም ከተለመደው የሰራ ሰዓት ውጪ ቀደም ብሎ ስራ የመጀመር እኒሁም አርፍዶ የመዝጋት ሙሉ መችት አለው። ኩ.ኤፍ.ዜት ሁኑንም ወላጆች ስለ ፍላጆታቸው ያማከራል። ኩ.ኤፍ.ዜት ያሉትን አማራቾች ተሞድኩዞ፣ የትኛውን አገልግሎት በየትኛው ግዜ የትኛውን ፕሮግራም እደሚያቅርብ ይወስናል። ይህ ውሳኔ ያሉትን ባሎያውች ብዛት እና ሰዓታት ተሞርኩዞ የሚዘጋጅ ነው።

**ልጆ በትምህርት ቤት እረፍት ሳምንቶች ውስጥ ወደ ኩ.ኤፍ.ዜት መሄድ ይችላል?**

ተምህርት ቤቶች ለእለፍት በሚዘጉነት ግዜ፣ በኩ.ኤፍ.ዜት ውስጥ ከፊል ክትትል ይኖራል። በዚህ ውቅት የሚሰጠው ክትትል/አገልግሎት ከተለመደው የተለየ ሊሆን ይችላል።ልጆ በትምህርት ቤቶች እረፍት ግዜ ክትትል የሚያስፈልገው ከሆነ፣ ይህህን ሃበሬታ አስቀደመው በማሳወቅ፣ ይህህን የሚያመለክተውን ፎርም ሞልተው ወደሚመለከተው ኩ.ኤፍ.ዜት ማስገባት ይኖርቦታል።

ኪታ ብሬመን
መንግስታዊ የብሬመን ክልል ህጻት እና ቤተሰብ መዓከል

የፖስታ አድራሻ
Auf der Muggenburg 5
28217 Bremen

ስልክ
0421-361 5700
ፋክስ
0421-361 59771
ኢ-ሜል
office@kita.bremen.de
ድህረ-ገጽ
www.kita.bremen.de

**ኩ.ኤፍ.ዜቶች የሚዘጉት መቼ ነው?**

ትምህርት ቤቶች ለክረምት፣ በጋ እና ፋሲካ በሚዘጉበት ግዜ ኩ.ኤፍ.ዜት በዓመት ወስጥ ለአጠቃላይ 20 የስራ ቀናት ያህል ይዘጋል።ከነዚህ ቀናቶች ውስጥ ደግሞ 15ቱ በበጋ (**Schulferien**) ውስጥ ይሆናሉ። ተከክለኛውን ግዜያት በተመለከት ኩ.ኤፍ.ዜቶ ለወላጆች አስፈላጊዎን መረጃ ይሰጦታል።

ኩ.ኤፍ.ዜቶ መቼ እንደሚዘጋ እስከ 3ኛው ወር መጨረሻ ባለው ግዜ መለጃውን አስቀደመው ያገኛሉ።

በአንድ አካባኢ የምገኙ ኩ.ኤፍ.ዜቶች  አስቀድመው እርስ በእርስ ይነጋገራሉ። ሌላ አማራጭ ካለተነኘ፣ ልጆ ለአጭር ግዜ ወደ ሌላ ኩ.ኤፍ.ዜት መሄድ ይኖርበታል።

በአመት ወስጥ ለአራት ቀናት ያህል (**„Qualitätsentwicklungstage“** (**QE-Tage**)) ተብሎ የሚጠራ የእድገት እና ጥራት ልምምድ ይደረጋል. በነዚህ ሁለት ቀናት ውስጥ ባለሞያዎች ስልጠና እና ትምህርት የሚያገኙበት ነው። በ'ኩ.ኤ. - ቀናት ወስጥ ለህጻናቶቹ ክትትል አይኖርም እንዲሁም መውዓለ-ህጻናቱ ዝግ ነው። የ'ኩ.ኤ. - ወናት መቼ እንደሚውሉ ኩ.ኤፍ.ዜቶ ከወላጅ ኮሚቴ ጋር አብሮ በመወሰን አስወደሞ ወላጆችን ያሳውቃል።

In **ከቁጥጥር ውጪ በሆኑ ሁኔታዎች** ውስጥ ኩ.ኤፍ.ዜት መዓከሉ ሊዘጋ ወይም ከተለመደው ይስራ ሰዓት በተለየ መልኩ ሊያገለግል ይችላል። ይህ የሚያጋጥመው ሌላ የተሻለ አማራጭ ከታጣ ብቻ ነው። ለምሳሌ ከጤና - ሚኒስቴር አዲስ ህግ ከወጣ። ይህ አጋጣሚ ከተፈጠረ፣ ልጆ ወደ ሌላ ኩ.ኤፍ.ዜት መዓከል ምሄድ አይችልም፣ እርሶም ገንዘቦትን ማስመለስ አይችሉም።

ከዚሁም በተጨማሪ በኩ.ኤፍ.ዜት ውስጥ **የባለሞያዎች እጥረት** ሊያጋጥም ይችላል። ለምሳሌ ያህል በአንድ የኩ.ኤፍ.ዜት መዕከል ውስጥ የሚሰሩ ባለሞያዎች ነእንድ ግዜ ከታመሙ ወይም አድማ ከመቱ ይህ ችግር ሊያጋጥም ይችላል። ይህ ካጋጠመ የድንገተኛ ተጠሪ ፕላን ይዘጋጃል ወይም ለክክትትል ሰዓት ከተለመደው ወጪ ሊሆኑ ይችላሉ። የድንገተኛ ተጠሪ ፕላን ማለት ለምሳሌ:

- ሁሉም ህጻናት ወደ መዓከሉ መምጣት አይችሉም
- የስራ ሰዓታት ሊያጥሩ ይችላሉ
- አንድ ወይም ብዙ የመውዕለ-ህጻናት ግሩፖች ሊዘጉ ይችላሉ።

የኩ.ኤፍ.ዜት አላማ ልጆችን መጠበቅ እና ማስተማር ነው። ይህህን አላም ለማሳካት ደግሞ ህጻናትን መቀበል የሚቻለው እንደባለሞያዎቹ ብዛት እና አቅም ነው። በብሬመን ክልል ውስጥ ባለው የመውዓል-ህጻናት እና የሕጻናት ዕለታዊ ጥበቃ እና ክትትል ደንብ መሰረት: ምን ያህል ባለሞያዎች እንደሚያስፈልጉ ተመዝግቡዋል የኩ.ኤፍ.ዜት ስራ አፈጻጸም ለድንገተኛ እንቅስቃሴ እርመጃ ይውሰዳል። ምን ያህል ባለሞያዎች እንዳሉ ታይቶ፣ የተለያዩ ወሳኔዎችን በተግባር ላይ ያውላል:

1. ለህጻናት እድገት ታስበው የሚደረግጉ እንቅስቃሴዎች፣ ለምሳሌ ሽርሽር ወይም ጉብኝቶች ይሰረዛሉ።
2. የክትትል ሰዓታቱ ያጥራሉ፣ ወይም የጠዋት ክትትል ወይም የቀትር ክትትል የቋረጣል
3. ኩ.ኤፍ.ዜት የመውዓለ - ህጻናት ግሩፖችን ወይ የደባልቃል ወይ እንዳንድ ግሩፖች የሰረዛሉ።

ኪታ ብሬመን
መንግስታዊ የብሬመን ክልል
ህጻት እና ቤተሰብ
መዓከል

የፖስታ አድራሻ
Auf der Muggenburg 5
28217 Bremen

ስልክ
0421-361 5700
ፋክስ
0421-361 59771
ኢ-ሜል
office@kita.bremen.de
ድህረ-ገጽ
www.kita.bremen.de

## በቦታ መገኘት ምዝገባ እና ጠባቂ ገለሰብ

**ልጆ ውደ ኩ.ኤፍ.ዜት መመጣት ካልቻለ መን ማድረግ ይችላሉ?**

ኩ.ኤፍ.ዜት ልጆን ነጥሩ ሁኔታ ለማስተማር እና ለመከታተል እንዲያስችለው፣ ልጆ በተከታታይ ወደ ማዕል]ከሉ መምጣት አለበት። ልጆ በዕለቱ ወደ ማዕከሉ መመጣት ካልቻለ፣ ይህህን በፍጥነት ለኩ.ኤፍ.ዜት ማዕከሎ ማሳወቅ ግሬታ አለቦት። ልጆ ወደ መዓከሉ የማይመጣበትንም ምክኒያት ያሳውቁ፣ ለምሳሌ ልጆት ከታመመ

**ትምህርት ቤት ለጀመሩ ህጻናት የሚሰጠው ክትትል መቼ ነው?**

ትምህርት ቤት ለጀመሩ ህጻናት: ኩ.ኤፍ.ዜቶ ለእያንዳንዱ የትምህርት ቀን ያለውን የልጅን ሰዓታት ተመልክቶ ከእርሶ ጋር በመነጋገር ሰዓታቶቹን ያመቻቻል።

**የልጆን የክትትል ቦታ ማጣት ይችላሉ?**

አስፈላጊ በሆነ መክኒያት፣ የልጆን የክትትል ቦታ ሊያጡ ይችላሉ። አስፈላጊ የሆነ መክኒያት ለምሳሌ: የተስማሙበትን ነጥቦች ብተደጋጋሚ ችላ ይላሉ ወይም አያከብርሩም። ብዚህም ሁኔታ እንኳን አስፈላጊው ለህጻኑ የተሻለው አማራጭ ነው።

ኩ.ኤፍ.ዜት. የልጆን ቦታ ለሌላ ክትትል ለሚያስፈልገው ቤተሰብ ቦትዎን አሳልፎ ሊሰጥ የሚችልበት ምክኒያት ልጆ ከሁለት ሳምንት በላይ ካልመጣ እና እርሶም ምክኒያቱን ካላሳወቁ ነው።

ቦታውን አሳልፎ ከመስጠቱ በፊት ኩ.ኤፍ.ዜት እንሶን ለማግኘት ሙከራ ያደርጋል። ላዚህም ይህህን የሚያሳውቅ ደብዳቤ ይላክሎታል። ደብዳቤም እንደደረሶት ለማራጋገጥ፣ ፈርመው እንደገና ወደ ማዕከሉ ይልኩታል። ምክኒያቶን መናገር ያልቻሉበት ተቀባይነት ያለው ጉሳይ ከነበረ፣ ቦታዎ ይመለስሎታል።

**ኩ.ኤፍ.ዜት ማቋረጥ ከፈለጉስ?**

ልጆን በየወሩ መጨረሻ ላይ የማሰረዝ መብት አሎት። ከዛ በፊት ግን የኩ.ኤፍ.ዜት. ማዕከሎን 14 ቀናት አስቀደመው ማሳወቅ ይኖርቦታል። ልጆን ከበጋ እረፍት መጀመሪያ አስቀደመው ካሰረዙን፣ የተቀሩን ወራቶች ክፍያውን መቀጠል አለቦት። የማሰረዞ መክኒያት ገን ቤት እየቀየሩ ከሆነ ገን፣ ተጨማሪ ክፍያ መክፈል አይጠበቅቦትም።

ኪታ ብሬመን
መንግስታዊ የብሬመን ክልል
ህጻት እና ቤተሰብ
መዓከል

የፖስታ አድራሻ
Auf der Muggenburg 5
28217 Bremen

ስልክ
0421-361 5700
ፋክስ
0421-361 59771
ኢ-ሜል
office@kita.bremen.de
ድህረ-ገጽ
www.kita.bremen.de

**ከእርሶ ውጪ ልጅን ሌላ ሰው ሊያመጣው ወይም ሊወስደው ይችላል?**

ልጆ ከቤት ወደ ኩ.ኤፍ.ዜት ኣንዲሁም ከኩ.ኤፍ.ዜትወደ ቤት ሲሄድ፣ ነጻነት ስሜት ሊሰማው ይገባል። ስለዚህ ከኩ.ኤፍ.ዜት መዓከሎ ጋር እነዚን ነጥቦች አስቀደመው ይነጋገሩ:

- ልጅትን መቼ ሊያመጡ ይችላሉ?
- ልጅትን መቼ መውሰድ ይችላሉ?
- ከእርሶ ውጪ ማን ልጅትን ማድረስ ወይም መውሰድ ይችላል?
- ልጅትን መውሰድ የማይፈቀድላቸው ሰዎች እነማን ናቸው?
- ትምህርት ቤት ለሚሄዱ ህጻናት: ልጆ ብቻወን ወደ ቤት መሄድ ይችላል?

**በሽርሽር ወይም ከመዋያው ውጪ ለሚደረጉ እንቅስቃሴዎች?**

ልጆ በሽርሽር ወይም ከመዋያው ውጪ በሚደረጉ እንቅስቃሴዎች ላይ መሳተፍ እንዲችል፣ መስማማትን/ ፍቃዶን በጽሁፍ መስጠት ይኖርቦታል።

**በከባድ የአየር ሁኔታውች ላይ አስፋላጊው መንድን ነው?**

በብሬመን ውስጥ ስላሉ ከባድ የአየር ሁኔትዎች በሬዲዮ የሚተላለፉትን መረጃዎች እና ማስጠንቀቂያዎች ይከታተሉ። በከባድ ነፋስ ወይም በሚያንሸራትት የበረዶ ግዜ፣ ልጆ ወደ ኩ.ኤፍ.ዜት ላይመጣ ይችላል።

*ለበለጠ መረጃ „ለከባድ የአየር ሁኔታዎች የተዘጋጀ ማስጠንቀቂያ“ (Warnung bei extremer Wetterlage) የሚለውን መረጃ ከኩ.ኤፍ.ዜት ማዕከሎ ማግኘት ይችላሉ።*

## የመለማመጃ ግዜ

**በኩ.ኤፍ.ዜት ውስጥ የመጀመሪያው የመለማመጃ አካሄድ እንዴት ነው?**

ህጻናት አዲስ መዋይ/ምቆያ ቦታቸወን በደንብ መለማመድ አለባቸው። ኩ.ኤፍ.ዜት አዲስ የሚመጡትን ልጆች በጥሩ ሁኔታ መንከባከብ ይፈልጋል። ስለዚህም ሁኑም ጅማሪ ህጻናት በአንድ ግዜ የመለማመጃ ግዜ አይኖርራቸወም። አዲስ ጀማሊ ልጆች በኩ.ኤፍ.ዜት. ውስጥ በተለያየ ግዜ የሚጀምሩ ይሆናል። የመጀመሪያ ቀናቸው መቼ እንደሚሆን ከወላጆች ጋር በመነጋገር የሚወሰን ይሆናል።

ልጆ ከትትሉን የሚያገኘው ከ01.08 ጀምሮ ከሆነ፣ ክፍያው 01.08 ጀምሮ የሚከፈል ይሆናል። ልጆ ቅይቶ የሚጀምርም ከሆነ ክፍያው ከጀመረበት ግዜ ጀምሮ ይሆናል።

በመጀመሪያው የልምምድ ግዜያት፣ ልጆ የብቸኝነት ስሜት መሰማት የለበትም። ስለዚህ በቅርብ የሚያውቃቸው፣ የሚያምናቸው ሰዎች በአካባቢው ያስፈልጉታል። ለምሳሌ፣ ወላጆች።

ልጅን በደንብ ለማወቅ እና የተሻለውን መንገድ ለመምረጥ፣ በልምምዱ ግዜ የኩ.ኤፍ.ዜት ባለሞያዎች ብዙ ጥያቄዎችን ይጠጾታል እንዲሁም ከእርሶ ጋር በጥልቅ የነጋገራሉ።

ኪታ ብሬመን
መንግስታዊ የብሬመን ክልል
ህጻት እና ቤተሰብ
መዓከል

የፖስታ አድራሻ
Auf der Muggenburg 5
28217 Bremen

ስልክ
0421-361 5700
ፋክስ
0421-361 59771
ኢ-ሜል
office@kita.bremen.de
ድህረ-ገጽ
www.kita.bremen.de

## ወላጆች ትልቅ ሚና ይጫወታሉ

**ወላጆች እና ኩ.ኤፍ.ዜት እንዴት መተባበር ይችላሉ?**
የአላማችን መሰረት ከወላጆች ጋር ያለን ትብብር ነው።
ተከታታይ የወላጆች ምሽት እናዘጋለን። ኩ.ኤፍ.ዜት በየአመቱ፣ የልጆ እንቅስቃሴ እንዴት እንደነበር እንዲሁም ሁኔታዎች እንዴት እንዳሉ በግል ያናግሮታል።
የወላጅ ኮሚቴ የሚመረጠው ከወላጆች ውስጥ እና በወላጆች ነው። ኩ.ኤፍ.ዜት ከወላጅ ኮሚቴው ጋር ጥብቅ በሆነ መልኩ በመተጋገዝ ይሰራል። የምንከተለው የመመሪያ ደንብ „የብሬመን ቤተሰብ ማዕከል “ („Bremer *Richtlinien zur Zusammenarbeit mit Elterngremien“)* በደነገገው መስመር ስር ነው

## የጤና ክትትል

**የልጆን ጤንነት በተመለከተ ኩ.ኤፍ.ዜት ማወቅ ያለበት ነገር መንድን ነው?**
በኩ.ኤፍ.ዜት ስር የሚገኙ ህጻናት በሙሉ ጤናማ እንዲሆኑ እንፈልጋለን። የታዳጊዎች - ጤና - አገልግሎት (Kinder- und Jugendgesundheitsdienst) በዚህ መስመር ላይ የተባበረናል። እነዚህ ድርጅቶች ከብሬመን ጤና ሚኒስቴ ስር የሚንቀሳቀሱ ናቸው።
ለኩ.ኤፍ.ዜት መዓከሎ አስፈላጊ የሆኑ የልጆን የጤነንት ሁኔታዋች ይጻፉ:

- ልጆ ጤነኛ ነው ወይስ የጤና ችግር አለበት?
- የጤናው ችግር ከክትትሉ ጋር ሊቃረን ይችላል?
- ልጆ አለርጂ አለበት?
- የማይስማሙት የምግብ አይነቶች መንደን ናቸው?

ኩ.ኤፍ.ዜት የተሰጡትን መረጃዎች እና የውሉን ደንቦች ያከብራል።
**ልጆ መድሃኒት መውሰድ ካለበት፣ ክትትሉ ጋርስ እንዴት ይሆናል?**
ልጆ በተከታታይ መድሃኒት መውሰድ ይኖርበት ይሆናል። ለምሳሌ ከሃኪም የታዘዘለት ክንኒ። የኩ.ኤፍ.ዜት ባለሞያዎች መድሃኒት መስጠት እንደማይፈልጉ የመወሰን ሙብት አላቸው። መድሃኒቱን መስጠት የሚስማሙ ባለሞያዎች ግን መጀመሪያ አስቀደመው ከወላጆች ጋር በጥልቅ ሰለ መድሃኒቱ እና አወሳሰዱ የነጋገራሉ። እርሶም የመስማማት ወይም የመከልከል ሙብት አሎት።
መድሃኒቱን መስጠት የሚስማሙ ባለሞያዎች ግን መጀመሪያ አስቀደመው ከወላጆች ጋር በጥልቅ ሰለ መድሃኒቱ እና አወሳሰዱ የነጋገራሉ። እርሶም ባለሞያዎቹም ከተስማሙ፣ ይህንን የሚያረጋግጥ ሰነድ በመፈረም ለኩ.ኤፍ.ዜቶ ያስረክባሉ። ከዚህም በተጨማሪ የሃኪም ማራጋገጫ ያስፈልገናል። ለዚህም: *UK-FHB-Medikamentengabe in Kindertageseinrichtungen* የሚለውን ፍርሙላ ይምሉ። በአርሙላይ ላይ መስፈርት ያለባቸው ነጥቦች:

- መድሃኒቱ መን ይባላል?
- ልጆ በቀን ውስጥ ምን ያህል መድሃኒት መውሰድ ይችላል?
- ልጆ መድሃኒቱም መቼ እና እንዴት መውሰድ አለበት?
- መድሃኒቱ እንዴት እና የት መቀመጥ አለበት?

ኪ.ታ ብሬመን
መንግስታዊ የብሬመን ክልል ህጻት እና ቤተሰብ መዓከል
የፖስታ አድራሻ
Auf der Muggenburg 5
28217 Bremen
ስልክ
0421-361 5700
ፋክስ
0421-361 59771
ኢ-ሜል
office@kita.bremen.de
ድህረ-ገጽ
www.kita.bremen.de

- መድሃኒቱ መን አይነት ሳይድ - ኢፌክት ሊኖረው ይችላል?
- የኩ.ኤፍ.ዜት አደጋ ገዜ ተጠሪ ምን ማድረግ ይችላል?
- ጥያቄ ካለ የኩ.ኤፍ.ዜት መዓከል ማን ማናገር ይችላል (የልጆ ዶክተር ስም እና የስልክ ቁጥር )?

**ልጆ ተላልፊ በሽታ አለበት፣ ምን ማድረግ ይችላሉ?**

ልጆ ተላልፊ በሽታ ካለበት ወደ ኩ.ኤፍ.ዜት. መምጣት አይፈቀድለትም። ይህ ደግም ልን ተላልፊ እስከሆነበት ገዚ ደረስ ማለት ነው። ልጆ ወደ ኩ.ኤፍ.ዜት መዓከል ከመመለሲ በፊት አስቀደመው ከዶክተሮ፣ ከጤና ጣቢያ ወይም ከጤና ሚኒስቴር፣ ተላላፉ እንዳልሆነ የሚያረጋግጥ ሰነድ ማቅረድ አለቦት። ይህህን ካረጋገጡ በውሃላ ልጆ ወደ ኩ.ኤፍ.ዜት መመለስ ይችላል።

ለበለጠ መረጃ *„Informationen zum Impfschutz und zum Infektionsschutz in Kindertageseinrichtungen"* የሚለውን ጽሁፍ የመልከቱ።

**ኩ.ኤፍ.ዜት እንዴት ለልጆ ጤናማነት እንቀሳቀሳል?**

ልጆ ማንኛውንም የበሽታ ምልክት ካሳየ፣ ኩ.ኤፍ.ዜት በአስቸኳይ ይደውልሎታል። እርሶም በተቻለ ፍጥነት ልጆን ከማዕከሉ መውሰድ አለቦት።

ብዚህ ሁኔታ ውስጥ ኩ.ኤፍ.ዜት እርሶን ማግኘት ካልቻለ፣ ልጆን ወደ ህክምና ባለሞያ የመድረስ መብት አለው።

**ልጆ ወደ ኩ.ኤፍ.ዜት ይትኞቹን ምግቦች ይዞ መሄድ ይችላል?**

ልልጆ ከቤት ምግብ ሊያስሩለት ይፈልጉ ይሆናል። ከቤት ምግብ ሊያዘጋጁለት ከፈለጉ፣ ከታች የተጠቀሱንት ህጎች ይከተሊ

ልጆ ይዞት መምጣት የማይፈቀደለት የምግብ አይነቶች:

- ጥሬ ስጋ (ለምሳሌ: ሜት፣ ሃከፔተር ወይም ታርታር)
- ጥሬ የተፈጨ ዉርስት (ለምሳልሌ: ስቪብልቩርስት፣ ቲቩርስት፣ ብራውንሽቫገር)
- ትኩስ ውተት ወይም የትኩስ ወተት ተዋጽዖ (ለምሳሌ፣ ከወተት የሚሰራ የዳቦ ክሬም)
- በደንብ ያልበሰለ ስጋ (ለምሳሌ ሜትቦልስ ወይም ፍሪካዴለ)
- ጥሬ ወይም በደንብ ያልበሰለ አሳ (ለምሳሌ፣ የላክስ ወይም ሳልሞን አይነቶች፣ ሱሺ)
- ያበሰለ እንቁላል ወይም ባልበሰል እንቁላል የሚዘጋጁ ምግቦች (ለምሳሌ ጣፋጮች ወይም ማዮኔዘ)
- የቀለጠ ወይ ቀልጦ እንዳዲስ በረዶ ውስጥ የተከተተ አይስክሬም
- የዶሮ ሰላጣ
- በአንድ በኩል ብቻ በስለው በሌኛው ያልበሰሉ ምግቦች (ለምሳሌ ቶርታ ኬክ)

*ለበለጠ መረጃ BIPS (Leibniz-Institut für Präventionsforschung und Epidemiologie) የሚለወን ጽሁፍ ይመልከቱ። የወላጆችን መረጃ ወረቀቶች ከኩ.ኤፍ.ዜት ማግኘት ይችላሉ።*

ኪታ ብሬመን
መንግስታዊ የብሬመን ክልል ህጻት እና ቤተሰብ መዓከል

የፖስታ አድራሻ
Auf der Muggenburg 5
28217 Bremen

ስልክ
0421-361 5700
ፋክስ
0421-361 59771
ኢ-ሜል
office@kita.bremen.de
ድህረ-ገጽ
www.kita.bremen.de

# ክትባት

**ኩፍኝን በተመለከተ ስላሉ ክትባቶች ማወቅ ያለቦት ምንደን ነው?**

ሁሉም ህጻናት ኩፍኝን ለመከላከል ክትባት መወሰድ አለባቸው። ክትባቱን መወሰዳቸውን ደግሞ ደ ኩ.ኤፍ.ዜት ከመመጣታቸው በፊት ማረጋገጫ ሊኖራቸው ይገባል። የኩፍኝ መከላከያ ደንድ ተላላፊ በሽታዎችን ለመከላከል በአንቀጽ § 20 ላንደተወሰነው ነው። የኩ.ኤፍ.ዜት መዓከሎን ይህንን ማራጋገጫ ማሳየት አለቦት። ይህ ማገጋገጫ፣ ከዶክተር ወይም ከጤና ባለሞያዎ መምጣት አለበት።

በኩ.ኤፍ.ዜት. ውስጥ ከ3 ቀናት በላይ የሚንቀሳቀሱ ወይም ለተወሰነ ደቂቃዎች የሚንቀሳቀሱ ሰዎች ይህንን ማረጋገጫ ማሳየት አለባቸው። ይህ ለወላጆች፣ ለጎብኚዎች እንዲሁም በድርጅቱ ውስጥ በማንኛውም ምክኒያት ለሚገቡ ለሚወጡ ሰዎች የሚመለከት ነው።

ክትባት ማረጋገጫ ማቅረብ የሌለባቸው ሰዎች:

- ክትባት የማይስማማቸው ግለሰቦች.
- ኩፍኝ ኖሮዋቸው የሚያቅ እና ስለዚህ ክትባት የምያስፈልጋቸው ግለሰቦች

ከላይ የተጠቀሱት ግለሰቦች የህክመና ማረጋገጫ ማቅረብ አለባቸው።

የኩፍኝ መከላከያ ክትባት እንዳልወሰዱ ማረጋገጫ ከሌሎት መዓከሉን መጎብኘት አይችሉም። ኩ.ኤፍ.ዜት መዓከሉም እርሶንም ልጅንም ለጤና ሚኒስቴር ማስመዝገብ አለበት። ለዚህም ስሞን፣ አድራሻዎን ለጤና ሚኒስቴ ይተላለፋል

**ሰለ ክትባት ምክር ማወቅ ያለቦት ነገሮች መንድን ናቸው?**

ከክትባት ጋር በተያይዘ ማወቅ ያለቦትን ነገሮች ከባለሞያ ጋር መነጋገሮን የሚያሳዉቅ ወረቀት ወይም ማርጋገጫ ለ ኩ.ኤፍ.ዜት ጽህፈትቤቶ ማስተላለፍ ይሮርቦታል። ይህንን ምክር አገልግሎት ከልጀ የጤና ባለሞይያ ማግኘት የሚችልኑ ሲሆን ወረቀቱ ከሌሎት ልጆን ወድኛ መላክ አይችሉም። እንደ ማረጋገጫ የሚያገለግሉ ነገሮች ከታች እንደተጠቀሱት ናቸው:

- ቢጫወን የህጻናት የጤና ምርመምራ ደብተር ወይም
- ይልጅን ይክትባት ማረጋገጫ
- ከሃኪም ቤት ወይም ከልጆ ዶክተር የተጻፈ ክትባት ማብራሪያ እንደተሰጦት የሚያረጋገጥ የጤና ማረጋገጫ

ማስረጃ ካልፈለጉ፣ ኩ.ኤፍ.ዜት የጤና ሚኒስቴረን ማሳወቅ አለበት፣ እዛ ላይ የኩ.ኤፍ.ዜት - ትብብር እንዳለ በማሳወቅ፣ ስም፣ አድራሻ እና ስልክ ቁጥሮን ለጤና ሚኒስቴር አስተላልፎ ይሰጣል። ይህ በህግ የተወሰነ ደንብ ነው።

ይህንን ማስረጃ ከመጀመሪያው ቀጠሮ ጀምሮ በውሃላ ባሉት 4 ሳምንታት ወስጥ ካልቀረበ፣ ኩ.ኤፍ.ዜት  የጤነ ሚኒስቴን ማሳወቅ አለበት/ ያሳውቃል።

ኪ.ታ ብሬመን
መንግስታዊ የብሬመን ክልል
ህጻት እና ቤተሰብ
መዓከል

የፖስታ አድራሻ
Auf der Muggenburg 5
28217 Bremen

ስልክ
0421-361 5700
ፋክስ
0421-361 59771
ኢ-ሜል
office@kita.bremen.de
ድህረ-ገጽ
www.kita.bremen.de

## ኢንሹራንስ

**ልጆ ኢንሹራንስ አለው?**

ልጆ በክትትል ወስጥ ባለበት ሰዓታት ኢንሹራንስ አለው፣ ይሕ የኣደጋ ኢንሹራንስ ነው። በየተኛው ቦታ እና ሰዓት ልጆ ኢንሹራንስ እንዳለው በዝርዝር በማህበራዊ ህግ *VII* እና ደንብ መጸሃፍ ውስጥ ተመዝግቡዋል። በማህበራዊ ህግ እና ደንብ መጸሃፍ ውስጥ የተመዘገቡት ህጎች እንደሚቀጥለው ናቸው

**ልጆ በየትኛው ቦታ እና ግዜ ኢንሹራንስ አለው?**

- ከቤት በቀጥታ ወደ ኩ.ኤፍ.ዜት ሲሄድ.
- ከኩ.ኤፍ.ዜት በቀጥታ ወደ ቤት ሲሄድ.
- ክትትል እየተደረገለት ባለ ግዜ.
- በኩ.ኤፍ.ዜት የተዘጋጁ እንቅስቃሴዎች ላይ ሲሳተፍ፣ በኩ.ኤፍ.ዜት ቅጥረ ግቢ ውስጥ ወይም በኩ.ኤፍ.ዜት ስር የተዘጋጀ ሽርሽር ላይ

**ልጆ ወደ ኩ.ኤፍ.ዜት ሲሄድ፣ ሲመለስ መንገድ ላይ የሆነ አደጋ ከደረሰበት ምን ማድረግ አለቦት?**

ኩ.ኤፍ.ዜት ውስጥ ሊያጋጥሙ ነገሮች በፍጥነት ባለሞያዎቹን ያናግሩ። ኩ.ኤፍ.ዜት በፍጥነት ጉዳዩን ለሚመለከተው ኢንሹራንስ ያመለክታል።

**ልብስ እና ሌሎች ንብረቶች በኢንሹራንሱ ስር ይጠቃለላሉ?**

ኩ.ኤፍ.ዜት ለሚከተሉት ነገሮች አይከፍለም:

- ልጆ ሌሎች ነገሮችን ከጣለ
- ልጆ ልብሱን ወይም ሌሎች ነገሮችን ከተቀየረ
- ልብስ ወይም ሌላ ነገር ክተበላሸ

## የወላጆች ተዋፆ

**የወላጆች ተዋፆ መንደን ነው?**

የብሬመን በመውዕለ - ህጻናት ወስጥ የሚገኙ ህጻናትን ማገገ እና ማበረታቻ መአከል ህግ እና ስርዓት መሰረት *በአንቀጽ § 19 ይዝባር 1* እንደተጻፈው: ወላጆች ልጃቸው/ልጆቻቸው ወደ ኩ.ኤፍ.ዜት ሲሄድ የሚገባቸወን የወላጆች ተዋጾ መክፈል አለባቸው። የወላጆች ተዋጾ በኣመት 12 ግዜ የሚከፈል ነው። ይህ ማለት በየወሩ የውላጅ ተዋጾ መክፈል ይኖርቦታል። የመጀመሪያውን የወላጅ ተዋጾ በኦገስት ላይ ይከፍላሉ። የመጨረሻውን የመውዓለ-ህጻናት አመት ተዋጾ ደግሞ በቀጣዩ አመት ጁላይ መጨረሻ ላይ ይከፍላሉ። በመሃል፣ ልጆ የትምህርት እረፍት ግዜ ፕሮግራሙን ባይጠቀም እንኳን የውላጅ ተዋጾው በየወሩ መክፈል አለበት።

ኪ.ታ ብሬመን
መንግስታዊ የብሬመን ክልል
ህጻት እና ቤተሰብ
መዓከል

የፖስታ አድራሻ
Auf der Muggenburg 5
28217 Bremen

ስልክ
0421-361 5700
ፋክስ
0421-361 59771
ኢ-ሜል
office@kita.bremen.de
ድህረ-ገጽ
www.kita.bremen.de

**የወላጅ ተዋፆዎን የት ነው የሚከፍሉት?**

ብሬመን የከትትሉን ክፍያ በሚመለከት ይህንን ስራ ወደ ፐርፎርማ ኖርድ (Performa Nord) ወደሚባል ድርጅት አስተላልፎዋል። ወርሃዊ ክፍያዎን በቀጥታ ወደ ፐርፎርማ ያስተላላፉሉ።

**የወላጆች ተዋፆ ምን ያህል ነው?**

የወላጆች ወርሃዊ ክፍያ የተለያየ ሊሆን ይችላል። የተዋጾን ከፍ ወይም ዝቅ ማለት የሚወሰነው:

- *አንቀፅ § 19 ይዝባር 1 ኣስከ 4 እና አንቀፅ § 20 በብሬመን ክልል ወስጥ ባለው ስለመዋዕለ - ህጻናት እድረት የሚመለከት ህግና ደንድ መሰረት ዕለታዊ ድርጅቶች፣ ዕለታዊ ጥበቃዎች*
- *አንቀፅ § 1 ይዝባር 3 የመዋዕለ ህጻናት አሰራር ደንብ*

## የግል መረጃዎች

**ኩ.ኤፍ.ዜት ስለእርቾ ያለውን መረጃ ማን ያደርገዋል?**

ኩ.ኤፍ.ዜት ስለ እርሶ እና ልጆ መረጃዎች ይሰበስባል። የሚሰበሰቡት መረጃዎች ግን በህግ የሚፈቀዱን ብቻ ነው። ከሚሰበሰቡት መረጃዎች ውስጥ አንዛኛዎቹ ለልጆ ጥበቃ እን ክትትል አስፈላጊ የሆኑትን ነው። ሌሎቹ ደገም በህግ ግዴታ የሚያስፈልጉ ናቸው። ለማንኛውም ጥያቄዎች ከታች የተሰጥውን ድህረገጽ ይመልከቱ

*ለበለጠ መረጃ [www.kita.bremen.de/datenschutz](www.kita.bremen.de/datenschutz). ድግረ-ገጽ ይመልከቱ።*

**በኩ.ኤፍ.ዜት ውስጥ ፎቶ ማንሳት፣ ቪድዮ፣ ድምጽ መቅዳት ይፈቀዳል ወይ?**

በኩ.ኤፍ.ዜት ውስጥ ፎቶ ማንሳት፣ ቪድዮ፣ ድምጽ መቅዳት እንዲሁም በተለያዩ መንገዶች እነዚህን መረጃዎች ማካፋል የሚፈቀደው የሚመለከታቸው ግለሰቦች ከተስማሙ ድቻ ነው።

ወላጆችም ቢሆኑ ሌሊች ልጆች በኩ.ኤፍ.ዜት ውስጥ የሚታዩበት፣ የሚሰሙበትን ፎቶ ማንሳት፣ ቪድዮ መቅረጽ፣ ድምጽ መቅዳት የሚችሉት የልጆቹን ቤተሰቦች አስፈቅደው፣ ወላጆቹም ከተስማሙ ነው።

## ኩ.ኤፍ.ዜት ውስጥ ስለሚዘጋጁ ሌሎች ፕሮግራሞች

**ሌሎች ሰዎችም ኩ.ኤፍ.ዜትን መጠቀም ይችላሉ?**

ኩ.ኤፍ.ዜት ለቤተሰቦች የታሰበ ወይም የተዘጋጀ ቦታ ነው። ስለዚህም በአካባቢው የሚኖሩ የምህበረሰቡ አባላት ኩ.ኤፍ.ዜትን መጠቀም ይችላሉ።

ለምሳሌ ያህል፣

- ተሸካሚው, ህጻናትን፣ ታዳጊ ወጣቶችን እና ቤተሰቦችን የሚያበረታቱ
- ተሸካሚው, ባህልን የሚያበረታቱ
- ተሸካሚው, ስፖርትን የሚያበረታቱ

ህጉን እና ወጪውን የሚወስነው ኪታ ብሬመን ነው።. ለዚህም የተዘጋጁ የአገልግሎት እና የክራይ ውል ሰነዶች

ኪታ ብሬመን
መንግስታዊ የብሬመን ክልል
ህጻት እና ቤተሰብ
መዓከል

የፖስታ አድራሻ
Auf der Muggenburg 5
28217 Bremen

ስልክ
0421-361 5700
ፋክስ
0421-361 59771
ኢ-ሜል
office@kita.bremen.de
ድህረ-ገጽ
www.kita.bremen.de

አሉ።

ኩሽናው እና በኩሽናይ ወስጥ የሚገኙት ንብረቶች መጠቀም ክልክል ነው። የኩ.ኤፍ.ዜት ሰራተኞች ክትትሉ በጥሩ እና ስነስርዓት ባለው መልኩ እንዲንቀሳቀስ ይጥራሉ። ያለዓግባባ ግን ለሰራተኞቹ ተጨማሪ ስራ መተው ተገቢ አይደለም።

## ተግባር ላይ መዋል

እነዚህ ህጎች ከዚህ ሰዓት ጀምሮ በተግባር ላይ ይውላሉ።

ኪታ ብሬመን
መንግስታዊ የብሬመን ክልል
ህጻት እና ቤተሰብ
መዓከል

የፖስታ አድራሻ
Auf der Muggenburg 5
28217 Bremen

ስልክ
0421-361 5700
ፋክስ
0421-361 59771
ኢ-ሜል
office@kita.bremen.de
ድህረ-ገጽ
www.kita.bremen.de

*[Übersetzt in die Sprache Amharisch]*